# የፕሮስቴት ነቀርሳ



ፕሮስቴት ከወንድ ልጅ ፊኛ በታች የሚገኝ፣ ለወንድ ዘር የሚሆን ፈሳሽ የሚያመርት እጢ ነው።

በሁሉም ዕድሜ ውስጥ ከሚገኙ፣ በካንሰር ምክንያት ከሚሞቱ ወንዶች ሶስተኛው ታዋቂ ምክንያት የፕሮስቴት ነቀርሳ ነው። ዕድሜያቸው ከ 40 በታች በሆኑ ወንዶች ላይ ብዙ የሚታይ የይደለም።

ፕርስቴት ነቀርሳ ባለባቸው ወንዶች ላይ ያለው ፕሮስቴት ስፐስፊክ አንቲጀን (prostate specific antigen) (PSA) በመባል የሚታወቀው ንጥረ ነገር አብዛኛውን ግዜ ከፍ ያለ ነው። ቢሆንም፣ የ PSA የደም መርመራ ውጤት፣ በሌሎች የፕርስቴት ሁኔታዎች ላይም ከፍ ሊል ይችላል። ይህም በኢንፈክሽንና በፕሮስቴት ማበጥ።



ሳይንቲስቶች የፕሮስቴት ነቀርሳ ምርመራን አስመልክቶ በየግዜው ተጨማሪ እውቀት እየቀሰሙ ናቸው። ለእርስዎ የተሻለው መቼና፣ ምን አይነት የ PSA ምርመራን ጨምሮ፣ የትኞቹን የፕሮስቴት ነቀርሳ መርመራዎችን ማድረግ እንደሚሻል ለማወቅ ሐኪምዎን ያናግሩ።

የ PSA ምርመራ በጣም እየተዘወተረ በመምጣቱ፣ አብዛኛው የፕሮስቴት ነቀርሳ፣ በሽታ ምልክት ከማሳየቱ በፊት ነው የሚገኘው።

ፕሮስቴት ካንሰር ብዙ ምልክቶች አሉት። ከዚህ የሚከተሉት ምልክቶች ካልዎት ሐኪምዎን ይዩ።



- ሽንትን ሲሸኑ መቸገር፣ እንደ ሕመም፣ ሽንት የመጀመር ችግር ወይም የማቆም ወይም ማንጠባጠብ ።
- ዝቅተኛ ጀርባ ህመም
- የወንድ ዘር ፍሬ በሚያፈሱበት ወቅት ላይ ህመም

ለፕሮስቴት ነቀርሳ የሚሰጥ ሕክምና የሚወሰነው ነቀርሳው ያለበት ደረጃ ታይቶ ነው። ነቀርሳው በምን ያህል ፍጥነት እያደገ እንደ ሆነና ባካባቢው ከሚገኝ ስጋ ምን ያህል ልዩ እንደሆነ ማወቁ ምን ደረጃ ላይ እንዳለ ለማወቅ ይረዳል።

- ህክምንናው ቀዶ ጥገናን፣ ራዲዬሽን ቴራፒን፣ ኪሞቴራፒ ወይም ነቀርሳውን ሊነኩ የሚችሉ ሆርሞኖችን መቆጣጠርን ሊያጠቃልል ይችላል።





**A project by Health Roads Media and EthnoMed**
This project has been funded in whole or in part with Federal funds from the Department of Health and Human Services, National Institutes of Health, National Library of Medicine, under Contract No. HHS-N-276-2011-0008-C with the University of Washington. Thank you to Safeway Foundation for its support to Harborview Medical Center's EthnoMed for the development of cancer-related content.

www.healthyroadsmedia.org and http://ethnomed.org
Prostate Cancer – Amharic (last reviewed June 2013)